# ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም

## ትዕይንት አንድ

1. / ከአንድ ዘመናዊ በሆነ ቪላ ቤት በረንዳ ግቢ/

1.1 / ከግቢ ውስጥ የተዋበ መናፈሻ፥ ከመኪና ማቆሚያ ውስጥም ዘመናዊ የሆነች የቤት መኪና እንደቆመች አዝግሞት እቦታው.../

1.1.1 / የሞባይል የስልክ ጥሪ ይሰማል/

1.2 / ከቪላ ቤቱ በረንዳ ላይ

1.2.1 / ብርሃኑ (ቤሪ) እድሜው በአርባ አምስት አካባቢ የሚገመት ጎልማሳ ሲሆን... አጠቃላይ ሁኔታው ግን ወጣት ነኝ የሚል እና...እንደ ዋናዎቹ ሙዚቀኞች ከጆሮው ላይ ሎቲ ከማድረግ አንስቶ የፀጉር አሰራሩም፥ በጂም አቆራረጡ እና በለበሰው ከነቴራ (ቲ ሸርት) እና ቁምጣ ሱሪ የተቀናጣ ሲሆን ...ወደ ፊትና ወደ ኋላ በሚንቀሳቀስ የመዝናኛ ወንበር ላይ ተቀምጦ ከጭኖቹ ላይ እድሜዋ በአርባዎቹ መጨረሻ ላይ የምትገኘውንና የማትመጣጠነውን ሴት አስቀምጦ እየተጎነታተሉ ሲሳሳቁና ሲያወሩ ይታያሉ። ቤሪ ከንፈሩን አሞጥሙጦ ይጠጋል / ከነሱ ፈንጠር ብሎ ካለው ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጡት ሦስት እጅግ ዘመናዊ ከሆኑ የሞባይል ስልኮች ውስጥ ከላይ የጥሪ ድምጽ ማሰማት የጀመረው ስልክ ለሦስተኛ ጊዜ ይጠራል መጥራቱንም ይቀጥላል።/

ቤሪ - የቤቲን ከንፈር ለመሳም ከንፈሮቹን አሞጥሙጦ እንደ ተጠጋት ስልኩ ለሦስተኛ ጊዜ በመጥራቱ ስላቋረጠው ብስጭት ብሎ /አ. ወ. ወ. ሺት... አምጭልኝ እስቲ ይሄን ምቀኛ/

ቤቲ - /ከወንበሩ ላይ እየተነሳችና እየሳቀች / ምቀኛ?!

ቤሪ - እንዴታ (አፍ ኮርስ) !!

ቤቲ - / ወደ ጠረጴዘው ሄዳ ከስልኮቹ መሃል የሚጮሀውን ለመለየት አነንብሳ እያየች /

ኸረ ቤሪ በጣም የምትወደውና የምታፈቅረው ሰው ቢሆንስ?

ቤሪ - ካንቺ በላይ የማፈቅረው?! በጭራሽ ቤቲ

ቤቲ - /የጥሪ ድምጽ ማሰማት የቀጠለውን ስልክ አፈፍ አርጋ እያነሳች/ በጭራሽ?!

ቤሪ- ያ!

ቤቲ - /ስልኩን ላለመስጠት እንዳሰበች ወደ ኋላዋ ይዛው ቆመች / እሺ እንደዚያ

ከሆነ ለምን ሁሉንም ስልኮች አትዘጋቸውም?

ቤሪ - እባክሽ ቤቲ የቢዝነሶቼን ጉዳዮች እያወቅሻቸው! ስልኮቹ ተዘጉ ማለት እኮ በየደቂቃ

የማገኘውን ገንዘብ ሁሉ አጣሁ ማለት ስ. ለ. ሆ. ነ

/ እጁን እየዘረጋላት/ እባክሽ

/ መሸጋገሪያ ሙዚቃ ይገባል/

ቤቲ - / ትጠጋውና ስልኩን ከመስጠቷ በፊት ጎንበስ ብላ ታናግረዋለች፡፡ ከዚያም ስልኩን

ትሰጠዋለች ጉንጩ ላይም ስማው ወደ ሳሎኑ በር ዞራ በመሄድ በሩን ከፍታ ትገባና

ትሰወራለች፡፡

ቤሪ - /ከተቀበለው ስልክ ላይ/ የደዋዩን ስምና ስልክ ቁጥር ይመለከትና የድምጽ

ማጥፊያውን ቁልፍ ተጭኖ ስልኩን ይዘጋዋል፡፡/

# ትዕይንት ሁለት

2. /ከዚያው ግቢ ውስጥ ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ/

2.1 / ከግቢው በር ላይ/

2.1.1 / የግቢው በር ከውስጥ በኩል እየታየ የመጥሪያ ደወል ይሰማል/

ዘበኛ - / ከመናፈሻው አካባቢ ወደ ግቢው በር በሩጫ አርምጃ እየተራመደ ይሄድና
የግቢውን በር ከፍቶ አንገቱን በማስገባት ከውጭ የቆመውን ሰው ያናግራል።/

2.2 / ከበረንዳው ላይ/

ቤሪ - / አስቀድሞ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ እንደ ተቀመጠ የሙዚቃ ማዳመጫውን
ከጆሮው ላይ ሰክቶ በሚያዳምጠው ሙዚቃ ከወንበሩ ጋር ወደ ፊተና ወደ ኋላ
እየተወዛወዘ አስቀድሞ የለኮሰውን ሲጋራ (ቶስካኖ) ያጨሳል።/

ዘበኛ - / ከግቢው በር ሮጦ ይገባና ወደ በሩ ብዙም ሳይጠጋ አንገቱን አስግጎ ጋሼ ... ጋሼ !

ቤሪ - /መለስ ብሎ ያየውና የጆሮ ማዳመጫውን ከጆሮው ላይ ነቅሎ እ.. ምነው?

ዘበኛ - / ወደ መግቢያው በር እየጠቆመ / አይ እንግዳ መጥቶ ነው

ቤሪ - / በመታሸት እየተወራጨ/ አ. አ. ወ - ሰውዬ! በዚህ ሰዓት ማንም ሰው ቢፈልገኝ
የለም እያልክ መልስልኝ አላልኩህም?

ዘበኛ - / በጣቶቹ ጸጉሩን እየቆፈረ/ እሱማ አ. ዎ ግን ለብርቱ ጉዳይ ነው ስላሉኝ እ. ና

ቤሪ - /አቋርጦት በማሾፍ/ ለብርቱ ጉዳይ?! /በንቀት/
ገንዘብ ለመለመን የመጣ ነው አትለኝም

ዘበኛ - ኧ. ረ -ጋሼ - የርስዎ - ማለት ወንድሙ ነኝ ብሎኛል

ቤሪ - /በድንጋጤ/ ወንድሙ ነኝ / እያሰበና በምጸት እየፈለገ

2.3 / ከግቢው በር ላይ/

ዘበኛ - / ከበረንዳው ወደ ግቢው በር እየሮጠ ሄዶ በሩን ይከፍታል

2.4 / ከበረንዳው ላይ/

ቤሪ - /አስቀድሞ ገብቶ በነበረበት ሳሎን ቀድሞ ከለበሰው ቁምጣ ሱሪና ከነቴራላይ የቤት ለቤት ልብስ ደርቦ መቀነቱን እያጠባበቀ በተከፈተው የሳሎኑ በር ወደ በረንዳው ሲወጣ ይታያል።/

በሪሁን - / እድሚያቸው በሃምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ የብርሃኑ ታላቅ ወንድም ሲሆኑ ኢትዮጵያዊ አለባበስ ለብሰው ከዘራቸውን ይዘው ከግቢው በር ወደ በረንዳው እየመጡ በነደደው ስሜት ምነው ... ምነው ልጄ በችግር ላይ መሆኔን እያወክ ... ስልክህን እንኳ አንስተህ ለማናገርም ቸገረህ?!

ቤሪ - አቤት አንተ ደግሞ ገና ከመምጣትህ ምንድን ነው ቁጣ ቁጣ?!

በሪሁን - ምነው አልቆጣ! ነው ወይስ ታናሽ ወንድሜም ስለ መሆንህ ልትክደኝ?!

ቤሪ - በጭራሽ

በሪሁን - / ገልመጥመጥ ብለው ያዩና/ እንግዲያውስ ...

ቤሪ - /አቋርጧቸው ወደ ወንበሩ እየጠቆሙ/ ለምን በመጀመሪያ አትቀመጥም

በሪሁን - / በምጸት/ ኧረ ግድ የለም ቆሜም በተሳካልኝ

ቤሪ - ምን ባለቤትህ ደህና አይደለችም እንዴ?

በሪሁን - እየነገርኩህ! ታማ የተኛችበትን የሀኪም ቤቱን የአልጋ ሂሳቡንም ሆነ ሌላ ሌላውን ሁሉ ለመክፈል አቅሜ እየተሟጠጠብኝ ስ. ለ. ሆ. ነ ካንተ ከወንድሜ በላይ የምጠይቀውም ሆነ የማስቸግረው ሰው የለኝምና ከጉድ አውጣኝ ብዬ ትናንትና ብነግርህ አ. ደ. ራ

ቤሪ - /አቋርጦት በመታሸት/ አ. አ. ዎ ያንተ ችግር እኮ አየህ ከጓሮዬ የብር ባህር ዛፍ የተከልኩኝ ይመስል አሁን ባሁን ጠይቀኸኝ አሁን ባሁን ካልወለደክ የማለትህ ነው

በሪሁን - / በምጸት ፈገግ እያለ/ አ. ሃ - ነው!!

ቤሪ - እ. ና ታዲያ ... ትንሽ ታገሰኝና ከጓደኞቼም ቢሆን አስፈልጌ እሸኝሃለሁ አልኩህ አ. ን. ተ. ግ. ን

በሪሁን - / በአሽሙርኛ ልሳን/ ኧረ በፍጹም ... እኔ እሺ እንኳንስ ለእኔ ለወንድምህ ይቅርና

ለማንም ትተርፋለህ ብዬ እ. ን. ጂ

ቤሪ - / በምጸት ፈገግ እያለ/ ለማንም ትተርፋለህ ?

በሪሁን - እና ታዲያ - እንግዲህ ጓደኞቼን እስክለምን ድረስ - አስጨንቄህ ከሆነማ /ወደ

ግቢው በር ዞሮ እየሄደ/ ግድ የለም ይቅርብኝ

ቤሪ - /አቋርጦት/ ቆይ - ቆይ እንጂ

በሪሁን - / በደረሱበት እየቆሙ እየዞሩ/ ስነግርህ! አዎን... እንግዲህ ልቦናህን አሳጥቶህ

ካልሆነ በስተቀር - " ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም" እንደሚባለው እውነት

ወንድሜን ቸግሮታል ብለህ ከልብህ ብታስብበት ኖሮ ለሀኪም ቤት የምከፍለውን

አይደለም ሀኪም ቤቱንም የምታስገነባበትንም ገንዘብ መኸረግ አድርገህ

መስጠት እንደምትችል ታውቀዋለህ። እና ግዴለህም ለባለቤቱም አንድዬ

መድኃኒዓለም ስላላት ላንተም ልቦና እንዲሰጥህ እለምንህልሃለሁ / እጅ እየነሱት/

ደህና ሁንልኝ የኔ ጌታ

ቤሪ - / በጭንቀት እየተወራጨ ሲያዳምጠው ቆይቶ ከበረንዳው ወርዶ ወደ ቸርነት ይሄዳል